# ፖለቲካ በደቦ - ክብር በአግቦ

ታሪኩ አባዳማ November 2007

ከመረጣቸው ሕዝብ ጎን ተሰልፈው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ምስረታ በመታገል ላይ ያሉት እና በህሊና እስረኝነት ከታገቱበት ነፃ የሆኑት ክብርት እና ክቡራን የቅንጅት ፓርቲ መሪዎች ወደ ሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ ለሥራ ከተሰማሩ ወዲህ በየዕለቱ የሚሰራጩ ዘገባዎች ፣ አስተያየቶች እና ቃለ መጠይቆች በአይነትም በይዘትም በርካታ ናቸው። እንደዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ዕምነት ፣ ዘገባዎቹም ሆነ አስተያየቶቹ ከፊሉ በቅንጅት አመራር አካል ውስጥ በውሳኔ አፈፃፀም ረገድ ልዩነት እንዳለ የሚያመለክቱ ሲሆኑ ቀሪዎች ደግሞ ፓርቲው እንደ ፖለቲካ አካል 'በቅጥረኛ እና ምንደኛ' እንደተጠልቀለቀ ብሎም ድርጅቱ እንዳበቃለት የሚሰብኩ ናቸው። 'ቅንጅት እገሌ ከሌለበት ቅንጅት አይደለም' ብቻ ሳይሆን እነ እገሌ 'ካልተመነጠሩ ፣ ካልተደመሰሱ' ድርጅት አይሆንም ተብለናል፤ ይህ ወይም ያኛው አቋም ከድርጅቱ የትግል መርህ ጋር አይጣጣምም ማለቱ ተዘንግቶ - እገሌ 'ስልጣን ጥመኛ ፣ ሌላው የዋህ አርበኛ' ተደርጎ ሲሰበክ ከርሟል።

በጥልቀት ሲመረመር የተከሰተውን ውስጠ ፓርቲ ችግር ባንድ ወገን መዓት እንደ መጣ ያህል እጅግ የከረረ ትርጓሜ ከ"ቆራጥ የመጠራረግ" መፍትሄ ጋር የሚመክሩ ወገኖች እንዳሉ ሁሉ ፓርቲው ፣ ቢያንስ ፣ የሚገዛበት መተዳደሪያ ደንብ ያለው እና ችግሩንም በዲሞክራሲያዊ ውይይት መቅረፍ እንደሚችል አበክረው የሚዘግቡ ደጋፊዎች በየረድፉ ታይተዋል። ታዲያ ችግሩ የሚፈታው በመርህ ላይ ተነተርሶ በአመራር አካሉ የሰከነ ውይይት ነው ወይንስ የፓርቲው ጉዳይ ጨርሶ የማይመለከታቸውን ግለሰቦች እና ቡድኖች ጨምሮ በደቦ እየተሰነዘረ ባለው ስድብ እና የእርግማን ዘመቻ ነው? ወያኔ ፣ ቅንጅት የተጎናፀፈውን ሕዝባዊ ክብር ያዋረደ መስሎት መሪዎቹን እና ደጋፊዎቹን በእስር እና ግድያ ያንገላታው ከቅንጅት የላቀ ሃያል ፣ እናም ቅንጅትን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት የሚያስችለው መስሎት እንደነበር የምንዘነጋው አይደለም። የመንፈስ ደካሞች ከነሱ ልቆ የሚታይን ሃይል የበለጡ መስሎ ለመታየት የሚጠቀሙት በሃይል ፣ በሀሰት ክስ እና በእመቃ ብቻ ለመሆኑ ዶ/ር መሳይ ከበደ ከጥቂት ወራት በፊት ያስነበቡን ትንተና ከዚህ ላይ ይጠቀሳል።

የቅንጅት አመሠራረት ታሪክ እንደሚያረጋግጠው በአመራር አካል ውስጥ ተመርጠው ያሉት ብዙዎቹ ግለሰቦች እርስ በእርሳቸው እንኳ የቆየ ግንኙነት ያልነበራቸው ይልቁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ይጋሩት የነበረው የዲሞክራሲያዊ ፓለቲካ ሥርዓት ጥማት ከተለያየ የሙያ ዘርፍ ፣ ፆታ ፣ ክልል ፣ የሕይወት ተሞክሮ አምጥቶ ባንድ እንዳስተሳሰራቸው እንገነዘባለን። እነ ሃይሉ እና ብርሀኑ ፣ እነ ብርቱካን እና እዮኤል ሌሎቹም ፣ የፍትህ - የርትዕ ጥያቄ አገናኝቷቸው በተማከለ የፖለቲካ ፕሮግራም እና ቃልኪዳን የተሳሰሩ ናቸው። በሕዝብ መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄ ላይ ያነጣጠረ ፓርቲ ሲመሠርቱ ፣ ፓርቲው የሚገዛበትን ደንብ ሲያረቁ እና ሲያፀድቁ ፣ የትግል ስልቱን ሲነድፉ እና ውሳኔዎችን በውይይት እና ድምፅ ብልጫ ሲወስኑ ብሎም የሥራ ክፍፍል ሲያደርጉ - ይህን በማድረጋቸው የተከተለውን የወያኔ ዱላ በጋራ ሲቋደሱ ፣ በእያንዳዳቸው ሕሊና ውስጥ ፅናት እና ቀናነት ያልተለየው አገርን የማዳን ተልዕኮ መሠረቱን እየጣለ ነበር።

ይህ በቅንጅት ምስረታ የተንፀባረቀ አንድነት የሕዝብን ተስፋ አለምልሟል ፣ ብሎም ተስፋው እውን እንዲሆን ሕዝብ በአንድነት አደባባይ ወጥቶ በጠመንጃ ፊት ሰላምን

እየዘመረ ተሰውቷል። በእምነት ዕዳ ፣ ለሕዝብ አለኝታ ለመሆን የተጠራሩት እንኝህ መሪዎች ለቆሙለት እና ለገቡት ቃልኪዳን ሲሉ እራሳቸውን ለመሰዋዕትነት ያቀረቡ ጀግኖች እንጂ ከማዶ ተቀምጠው የነፋሱን አቅጣጫ ሲያዳምጡ እና ሲዋዥቁ የነበሩ አይደሉም። ይህንንም ወያኔ የጠመቀውን የግፍ ፅዋ ከሕዝባቸው ጋር በመቃመስ አስመስክረዋል። ዛሬ ብዕራችንን አሹለን በነኝህ መሪዎች ላይ (አንዱን ወይም ሌላውን የወገንን አስመስለን) አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ የምናሰራጭ ወገኖች በደቦ እየወጋን ያለነው ጥንስሱን ሕዝባዊ ራዕይ ፣ ይህን የሕዝብ ደም እንጅረት የፈሰሰበትን ታሪካዊ ተልዕኮ ነው። ሃይሉን ወይም ብርሀኑን አይደለም።

የዲያስፖራው ፖለቲከኛ ለቅንጅት ችግር 'መፍትሄ' እጠቁም ብሎ ጥቂቱ አንዱን ጎራ በይፋ ወግኖ ሌላውን ጭልጥ ባለ ተራ የግለሰብ ስም ማጉደፍ ዘመቻ ሲያብጠለጥል ቀሪው ደግሞ የትግሉን አቅጣጫ ይበልጥ ለማጎልበት በአካል ሳይቀር ተገኝቶ ድጋፉን በጨዋ እና የሰለጠነ የፖለቲካ ወግ ሲደግፍ ታይቷል። የትኛው ጎራ ከየትኛው በቁጥር ይሁን በሌላ መመዘኛ ይልቃል የሚለውን እዚህ ማንሳት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም ፣ ለችግሩ መፍትሄ ስላልሆነ። ይሁንና በአንዳንድ አመራሩ አባላት እምነት ፣ ጥቃቅን ልዩነቶች አገርን ለመታደግ ከታለመው ግዙፍ ራዕይ አንፃር ሲታዩ ኢምንት መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ አቋሞች ሲንፀባረቁ ሰምተናል። ትኩረታችንን በዚህ አዎንታዊ ዝንባሌ ላይ ማድረግ ብንችል በጎ አማራጮችን መጠቀም የሚያዳግት አይሆንም ነበር።

እጅግ አድርጎ የሚያሳዝነው ግን ቅንጅትን ለመፍጠር ስንት ውጣ ውረድ ያሳለፉ ፣ በየትግል እርከኑ መራራ መስዋዕትነት እየከፈሉ ድርጅቱን ከሕዝብ ህሊና ሰርፆ እንዲገባ ያስቻሉ መሪዎችን 'አንቺ አንተ' እያሉ ለመወረፍ ሰፊ ዘመቻ የያዙት ወገኖች ለድርጅቱ መጎልበት አንዳች አስተዋፅኦ ያልነበራቸው ፣ ዛሬ ድረስ በድርጅቱ ዘንድ ምንም አይነት የስራ ድርሻ የሌላቸው ወገኖች መሆናቸው ነው። እንዲያውም እንኝህ ወገኖች መሪዎቹ ታግተው በነበረበት ጊዜ በየወቅቱ በቅንጅት ስም የሚተላለፉ አቋሞችን ሲያብጠለጥሉ የቆዩ ናቸው ብል ከእውነት የራቀ አይመስለኝም። ዛሬ ላንደኛው ወገን መሳፍንታዊ ክብር ያላቸው የሚመስሉት ሌላውን በማራከስ እና የሀሰት ክስ በመደርደር መሆኑን ስናስተውል - ለስድብ እና እንካሰላንቲያ የታጠቁ ወገኖች ውሎ አድሮ ለማንም የማይተኙ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባም። ሃይሉ ሻውልን ለማሞካሸት በትግል ሂደት ውስጥ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከበቂ በላይ ነው። ለሳቸው ክብር ለመጨመር ሲባል ግን የትግል ወንድሞቻቸውን ስም እያነሱ ከፖለቲካው ትግል ጋር አንዳችም ግንኙነት በሌለው ጉዳይ ላይ መወረፍ ትርፉ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚያዳግት አይደለም። የሞራል ዝቅጠት የሚንፀባረቅባቸውን እንኝህን አስተያየቶች በቅንጅት ስም በተከፈተ ድረ-ገፅ ላይ ጭምር አውጥቶ ስድቦችን ማስተጋባት "ከሰደበኝ ይልቅ የነገረኝ" የሚለውን ብሂል እንድናስታውስ ያደርገናል። አግቦ ለክብር መጎናፀፊያ ሆኖ አያውቅም።

ከዚህ አንፃር ጉዳዩ አሁን በምናየው መልኩ የተወሳሰበ አቅጣጫ እንዲይዝ ለማድረግ በቅንጅት ውስጥ ጭምር በተለያየ ግላዊ እና ቡድናዊ ፍላጎት ስር የተሰለፉ ሃይሎች የበኩላቸውን አላማ ለማሳካት ተግተው እየሰሩ መሆናቸው ሳይጠቀስ አያልፍም። እነኝህ ወገኖች ለገዛ አላማቸው አመቺ ይሆናል ብለው የገመቱትን ጉዳይ ፣ ኢምንት እንኳ ቢሆን ፣ ከአገር ዘላቂ ጥቅም አኳያ ክብደቱን ሳያመዛዝኑ ችግሮችን እየመዘዙ የሚያራግቡበት ሁኔታ በስፋት እየታየ ነው።

እነኝህ አፍራሽ አቋሞች ከፊሉ ቡድናዊ ቀሪው ተናጠል የሆነ ቅርፅ ያላቸው ቢመስሉም ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲያዊ ነፃነቱ የሚያከሂደው ትግል ከለየለት የወያኔ ጥቃት ባልተናነሰ ደረጃ ምንኛ በእሾህ የተከበበ መሆኑን ግን ይበልጥ ያረጋገጡ ሁነታዎች ናቸው። ወያኔ እንደ ፖለቲካ ሃይል ፣ የዲሞክረሲ ሥርዓት ግንባታውን ለማሽመድመድ የአፈና ተቋማቱን እየተጠቀመ ነው። የኛ ተግባር ሁሉም ዜጋ በላቀ የነቃ ተሳትፎ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሰረት ትግሉን ያለማወላወል ማገዝ መሆን ሲገባው ይህ ግን አየሆነ አይደለም። በዚህ ረገድ ባለፋት ሶስት ወራት ካንዳንድ የቅንጅት መሪዎች አንደበት የሰማናቸው ቅጥፈቶች ፣ ስድቦች እና እርግማኖች ታማኒነትን እጅግ አድርገው እንደሸረሸሩ መገንዘብ ያሻል።

ወያኔን በረገምንበት አንደበታችን የቅንጅትን መሥራች እና የአመራር አካል አባላት በጭፍን መወረፍ አንድም የምናራምደው ፖለቲካዊ አቋም ወጥነት ወይም ቀጣይነት የሌለው ብሎም የታማኒነታችን ጉዳይ ጥያቄ ላይ እንዲወድቅ የሚያደርግ ነው። እንደግፋለን የምንለውን ድርጅት መሪዎች በሀሰት ስንወነጅል ፣ እንጥለዋለን የምንለውን ወያኔ ለማውገዝ ምን ያህል እውነት ላይ ተመርኩዘን ነው የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል። ‘የኛ አቋም ካልሆነ ምርኩዛችን እውነት ይሁን ሃሰት ምን ተዳችን’ ያልን ይመስላል። ይህ ደግሞ የኔ የምንለውን ጥቅም የሚያስከብር ሳይሆን የለየለት ጠላት ብለን የፈረጅነውን ወያኔ ብቻ ነው የሚጠቅመው። ታማኒነት በፖለቲካ ትግል ውስጥ ፣ በተለይም በፕሮፖጋንዳው መስክ ቁልፍ መሳሪያ ነው። ፖለቲካ በስርዓት የሚመሰረት ፣ የሚመራ ብሎም የሚገዛ እንጂ ሆ ይህን አንሳ ! ሆ ይህን ጣል ! ሆ ወደ ፊት - ሆ ወደሁዋላ! የሚባል የደቦ ጥሪ አይደለም።

ሕዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በሃቅ ማስተጋባት ይኖርብናል። የምናቀርባቸው ክሶች እውነተኛነት የሚመዘነው አንድም ሕዝቡ በዕለት ህይወቱ የሚያየው ጉዳይ በመሆኑ ሲሆን ሌላው ግን የፕሮፖጋንዳ ስልታችን ታማኒነት እንዲያተርፍ የቱን ያህል እንጠነቀቃለን የሚለው ነው። በተቃዋሚ ፖለቲካ አቋማቸው ሕዝባዊ ሞገስ የተጎናፀፉ ግለሰቦችን ‘ባንዳ ፣ ከሀዲ…’ እያሉ ለመርገም መድፈር ‘ለካስ ሁልግዜም የሚያወሩት ሃሰት ነው’ የሚል ግምት ላይ ይጥላል። ምክንየቱም ሕዝብ እነኝህን ግለሰቦች የሚያውቃቸው በባንዳነት አይደለምና። በመጀመሪያው የትግል ረድፍ ላይ ቆመው ወያኔን ሲጋፈጡ ሕዝብ የሚያውቃቸውን መሪዎች ብድግ ብሎ ‘በከሀዲነት’ መፈረጅ እንዲህ ባዩን መሳለቂያ ከማደረግ ሌላ ክብር አያስገኝም። እነኝህ ተራጋሚዎች ከዚህ በሁዋላ ወያኔ እንዲህ ነው ቢሉ እንኳ ተቀባይነት ለማግኘት ቀላል አይሆንም። የሚያሰራጩት ወሬ ወይም ፕሮፖጋንዳ ተጨባጭነቱ አጠራጣሪ በሆነ መጠን የተደበቀ አጀንዳ ይዘው በማምታታት ለመጓዝ እያደቡ መሆኑን ያመለክታል። ወያኔም በበኩሉ እጁን አጣጥፎ አያይም - አሁን አፍቃሪ ወያኔ ድረ-ገፆች ላይ እየተደረገ እንዳለው እያንዳንዷን የደቦ ሴራ እየተነተነ የተሰበረውን የራሱን አቋም ይጠግንበታል።

በቅንጅት አመራር ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን ድርጅቱ ከተለመው ዲሞክራሲያዊ ራዕይ አንፃር መተቸት በተገባ ነበር ፤ አንዳንድ ድረ-ገፆች በየዕለቱ እንደሚያደርጉት ተራ ስድብ እና ፀያፍ አባባሎችን በመጠቀም የፖለቲካ ትርፍ ማግኘት የሚቻል ከሆነ ፍርዱን ከሕዝብ መጠበቅ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ የደቦ - አግቦ ዘመቻ ጉዳዩን ከሚያንገዋልሉት ከነኝህ ድረ-ገፆች ጀርባ ያሉትን ግለሰቦች የፖለቲካ

አስተሳሰብ ድህነት፣ የሃላፊነት ስሜት ማጣት ብሎም ለአገር ጉዳይ የሚሰጡት ግምት ምን ያህል ተራ እና ተርታ እንደሆነ መገንዘብ አስችሎናል። ብዕራችሁን አርቁ ብሎ ሃይ የሚላቸው የለም ወይ ብዬ ይጨንቀኝ የነበረው ፣ ሁዋላ እንደተገነዘብኩት ማንነታቸውን አመዛዝኖ የሚፈርድ ጨዋ ሕሊና ያለው ሕዝብ ባለበት አገር በተግባራቸው ይተፉ እንጂ ማን ከነሱ ጋር ግዜውን ያባክናል? እንዲያውም  የሁሉም ማንነት የሚመዘነው በአድራጎቱ እንደመሆኑ በቅንጅት ፓርቲ ውስጥ የተነሳው ውጥረት እንደነኝህ አይነቶቹን ወገኖች አበጥረን በነቂስ እንድንለይ ረድቷል እላለሁ። ዛሬ ስድብ እና አሉባልታ ፍለጋ የትኛውን ድረ-ገፅ መከፈት እንዳለብን ብዙ የምንቸገር አይመስለኝም። በስድብ እና እርግማን ቅኔ ተክነን ፣ በሃሰት እና ፈጠራ ወሬ ታጥቀን ወያኔን ቀርቶ ማንንም ከቆመበት ፈቅ አናደርግም። በደቦ ትግል አይመራም - በአግቦ ክብር አይገኝም።